# ይድረስ ለጦር ሀይሎች አባላት በሞላ ከኢሕአፓ

በዓለም ታሪክ እንደሚታወቀው በየሀገሩ ሊኖሩ የሚችሉ የጦር ሀይሎች ሁለት ዓይነት ናቸው-- ለገዢው ክፍል መሳሪያ ሆነው ለጭቆናው አገዛዝ ደጀን የሚሆኑና ህዝብን የሚጨፈጭፉ ወይም የህዝብና የሀገር አገልጋይ ሆነው ዳር ድንበር እየጠበቁና በዕድገቱ ጥረት እየተሳተፉ የሀገር ጦር የሚባሉ:: በሀገራችን ያልታደልን ሆነን አብዛኛውን ጊዜ የጦር ሀይሉ የገዢው ክፍል መሳሪያ ሆኖ በህዝብ ላይ በደልን እየፈፀመ ለጨቋኙ ስርዓት ዕድሜ ቀጣይ ሆኖ ቆይቷል:: ዛሬም የተለየ ክስተት የለም::

የአሁኑን ሁኔታ በተለይ ክፉ የሚያደርገው ገዢው ክፍል የራሱን ጦር ያውም በብሄረሰብ ደረጃ የተደራጀውን በሀገሪቷ ላይ ማስፈኑ ነው:: የድርጅት ጦር፣ የብሄረሰብ ጦር ለመሆኑ ደግሞ የሰሞኑ የጄኔራልና የኮለኔል ሹመት ራሱ ዳግም ያረጋገጠው ነው:: በመኪና፣ገንዘብ፣ሹመት፣ የመሬትና የቤት ስጦታ መኮንኖችን ከጎኑና ከስሩ አሰልፎ የመለስ አገዛዝ ዕድሜውን ለማራዘም እየጣረ ነው:: በተለይ በአሁኑ ጊዜ የመለስ ቡድን በፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ገብቶ ስለሚገኝ፣ ለባዕድ ቅጥረኛ ሆኖ ዘው ባለበት ሶማሊያም በቀላሉ ሊወጣበት የማይችል ረግረግ ሆኖበትና በሰሜን ደግሞ ሌላ ጦርነት ሊፈነዳ ያቆበቆበት ሁኔታ ላይ ነው:: ይህ ከባድ ቀውስ በተለይ በግንባር እየተጋፈጠና የህይወት ዋጋ እየከፈለ ያለውን የጦር ሀይል የሚመለከት ነው:: በሀገራችን የጦር ሀይል አባላት የህዝብ ጦር ለመሆን ጥረታቸውን ያደረጉበት ጊዜ አልነበረም ማለት አይቻልም:: በ1953 ዓ.ም. ጄኔራል መንግስቱ ንዋይና ሌሎች መኮንኖች መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ ሞክረው በህይወታቸው ከፍለዋል:: በሌሎች ሙከራዎች መክሸፍም የታሰሩና የተጋዙ ነበሩ:: በየካቲት 66 ም ቢሆን መኮንኖችና ወታደሮች ከጭቁኑ ህዝብ ጎን ተስልፈው ነበር:: ምርጦች የህዝብን ድል ቀምተው በስልጣን በተሰየሙበት ጊዜም የጭቁን ወታደሮች ድርጅት በሚል በጦሩም በአየር ሀይሉም ተሰባስበው ከህዝብ ጎን በመቆም መስዋዕትነት ከፍለዋል:: እነ ሻምበል አምሀ ፣ መቶ አለቃ መሀመድ አሊ፣ ወታደር ከተማ አባተ ፣ ወታደር ተስፋዬ ዳመሳ፣ ወታደር አብዲ ሰንደሎ፣ሻለቃ ሞገስና ሌሎችም ብዙዎች ሲሰዉ ሌሎች በርከታዎች ደግሞ ስቃይን በደርግ እስር ቤቶች ተቀብለዋል:: በትግል ሜዳም ወደ ታጋይ ሀይሎች እየተቀላቀሉ ለህዝብ የታገሉ ብዙዎች ናቸው:: ለስርዓቱ፣ለአገዛዙ ብቻ ታማኝ ክብር ዘበኛ ሆነው አላለፉም:: እነ ታየ ቶላ፣ እነ ህብስቱና ሌሎችም ምስክር ናቸው::

**የጦር ሀይሎች አባላት ሁሉ፣**

ዛሬ የንፁህ ዜጋ ደም በኦጋዴንና በሌሎችም ቦታዎች እየፈሰሰ ነው:: ከሁለት ዓመት በፊት የህዝብን ድምፅ የረገጠውና የሰረቀው አገዛዝ ፌዴራል ፖሊሶችን ተጠቅሞ ከሁለት መቶ በላይ ዜጎችን ጨፍጭፏል:: በጋምቤላ ፍጅት ተካሂዷል:: ከቋራ አርማጨሆ እስከ ባሌ ሀረርጌ ህይወት እየተቀጠፈ ነው:: የመለስ አገዛዝ ፀረ ህዝብ ለመሆኑ ለጦር ሀይል አባላት ቅስቀሳ አያሻም:: ጥያቄ ያነሱትን ገና ከስልጣን ሲደርስ በኢህዴን ጦር ላይ እንዳደረገው ሁሉ አፈና ያካሂድባቸዋል:: ዛሬ ግብዣውና ሹመቱና የገንዘብ ድጎማው ይህን ሀቅ የሚደብቅ አይደለም:: መለስ ዜናዊ የሚተማመነው በራሱ ምርጥ ሀይል ብቻ እንጂ በጦር ሀይሉ በተሰለፋችሁት ሁሉ ላይ እንዳልሆነም ነጋሪ አጋላጭ አይጠይቅም:: ስንቱ ተመንጥሯል? ተባሯል? ለስደት ተዳርጓል? በምስጢር እስር ቤቶች እንዲሚቀቁም ተደርጓል? ዛሬ በወያኔ ድርጅት አባልነት ሆነ በትግራይ ልጅነት ሹመት በሹመት የሆናችሁ መኮንኖች ነገ ቀውጢ ቀን ሲመጣ መለስ ዜናዊ ይዟችሁ የትም እንደማይሄድ ግልፅ ነው:: ግልፅ ካልሆነ ወደ ቃሊቲ ዕይታችሁን መልሱና የቀድሞውን አገዛዝ መኮንኖችን ዕጣ መመልከቱ ይበቃል:: ስለዚህም ከህዝብ ጎን በመቆም ታሪክን ማደስና ከወንጀልም መራቅ የሚገባ ነው:: ውሎ አድሮ በህዝብ የአመፅ ማዕበል አገዛዙ ተጠርጎና ተጠራርጎ መወገዱ የማይቀር ነውና ይህ አረመኔ አገዛዝ የሚሰጣችሁ ጥቅማ ጥቅም ሆነ ማዕረግና ሽልማት ለውንጀል ተባባሪነት ማረጋጋጫ ሆኖ ከመወሰድ የሚያመልጥ አይሆንም:: የህዝብ ፍርድ ሲመጣ ደግሞ የሚደበቅ ታሪክና ድርጊት የለም::

**የጦር ሀይሎች አባላት ሁሉ**

በሰሜኑ ለሞት የዳረጋችሁ የመለስ አገዛዝ ነው:: ሲከተለው የነበረው ፀረ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ሀገራችንን ገነጠጣለ፣ አልፎም አስደፈረ :: በህዝቦች መካካል ቅራኔ በሌለበት ገዢዎች በፈጠሩት ችግር ከመቶ ሺ ያላነሰ ወታደር አለቀ:: ምንስ ተገኘ ? መልሱ ከዕልቂት ሌላ ምንም ነው:: ያለፈው አልበቃ ብሎ ይኸው ለሌላ ዙር ጦርነትና ዕልቂት እያዘጋጃችሁ ነው:: በሶማሊያ የሚካሄደው ጦርነት የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅም ማስጠበቂያ አይደለም:: ከመጨረሻው የኦጋዴን ጦርነት በኋላ ያለፈው አገዛዝ ወታደሩን ሶማሊያ ከቶ ሳያስጨርስ የዚያድ ባሬን አገዛዝ ጥቃት በበቂ ሊከላከልና አልፎም ውድቀቱን ሊያፋጥን ችሎ ነበር:: መለስ ዜናዊ የጦር ሀይሉን ወደ ሶማሊያ አስገብቶ እያስመታ ያለው የሀገርን ጥቅም ለማስጠበቅ ሳይሆን ለአሜሪካ መንግስት ተልዕኮ ጀሌና ጭዳ ለመሆን ነው:: የሶማሊያን እርስ በርስ ጦርነት በተመለከተ ሆነ በኢትዮጵያ ላይ ሊመጣ የሚችለውን ጥቃት ለማስቆም የሰው ሀገር ወረራው ጠቃሚ ሳይሆን ጎጂ፣ ጠላት የተባሉትን የመከፋፍል ሳይሆን የሚያስተባብርና አደጋውንም የሚያባብስ ነው:: ይህም እየታየ ነው:: የዚህ መዘዝ የታያቸው ወታደሮች በየአቅጣጫው እየኮበለሉ ያሉት የጦር ሀይሉ አባላት ሀገራቸውን ጠልተው አይደለም:: ሀገሩን የወደደ ከመለስ ስር አይሰለፍም:: ሀገሩን የወደደ በመለስ ትዕዛዝ ንፁህ ዜጋን አይጨፈጭፍም:: ስለዚህም የጦር ሁሉ አባላት በያላችሁበት በአገዛዙ ላይ መነሳት አለባችሁ:: በቅርቡ በ4ኛ ክፍለ ጦር ያደረጋችሁት የተቃውሞ ስብሰባ ዓይነቱ መበራከት አለበት:: በመደራጀትም መታጀብ አለበት::

ተቃውሞን በግፍ አፋኝና ጨፍጫፊ የሆነ አገዛዝ በመስፈኑ ተገቢው ጥንቃቄና የአደረጃጀት ስልት አስፈላጊ ነው:: በቅድሚያ ጦሩን በብሄረሰብና በሀይማኖት ደረጃ ከፋፍሎታልና ይህን ማስወገድ፣መታገል ያስፈልጋል:: በዚህም በዚያም ግን የሚተማመኑ ሀገር ወዳድ መኮንኖችና ወታደሮች የስብስቡ ማዕከል ሆነው እንቅስቃሴውን መጀመር አለባቸው:: የዚህ እርሾ በየክፍለጦሩና ኮሩ መኖሩን ሳትገምቱ አትቀሩም:: ይህን እርሾ በየፊናችሁ ለማገዝ ከቅርባችሁና ከምታምኗቸው ጋር ሀሳብ ለሀሳብ በመለዋወጥና ቀስ በቀስም መረቡን ለማስፋት መጣር ይገባል:: የአገዛዙን ሰላዮችና ቅጥረኞች እንዲሁም ሰርጎ ገቦች በማራቅ:: ምስጢርን በመጠበቅና ለአገዛዙ ዝግ በመሆን:: ይህ እንቅስቃሴ እየተያየዘና በምስጢራዊ አወቃቀር ደግሞ ደህንነቱን እየጠበቀ ከሄደ ጦሩን ለመቀስቀስና  ከህዝብ ጎን ሆኖ ለሚወሰድ ወሳኝ እርምጃ ማዘጋጀትም ይቻላል:: አገዛዙ በንፁህ ዜጋ ላይ የሚወስደውን እርምጃ ማደናቀፍም ተገቢ ስራ ነው:: በህዝብ ላይ ሊዘምት ሲነሳ የዘመቻ ክንዱን ማድቀቅ ግዴታችሁ ነው:: በይፋ ከህዝብ ጎን ወጥታችሁ ጠመንጃችሁን በእነ መለስ ላይ እስክትወድሩ ድረስ የህዝብ የስውር ጦር ሆናችሁ አገዛዙን በማዳከም ከፍተኛ አስተዋፅዖ ለማድረግ ትችላላችሁ:: ይህንንም ህዝብ ያስታውሳል፣ ይክሳል፣ ይዘክራል፣ያመስግናል::

**ለጦር አባላት ሁሉ በያላችሁበት፣**

የትግል መስክ በሁሉም አቅጣጫ ነው:: ትግላችን ሁለገብ ነው:: ተቃዋሚ ሀይሎች ህብረታቸውን በአሁኑ ጊዜ አጠናክረው ለመገኘት ባይችሉም ትግሉ ይቆማል ማለት አይደለም:: ህዝብ አለ ፣ ለውጥና ዕድገትን፣ሰላምና ዴሞክራሲን ፈላጊ ህዝብ አለ :: ይህን ህዝብ ረግጠው የሚገዙት አረመኔዎች የሚመኩት በእናንተ ላይ ነው:: እናንት ግን ከህዝብ አብራክ የወጣችሁ ናችሁና በህዝባችሁ ላይ ለጥቂት አረመኔዎች ስትሉ ግፍ ልትፈፅሙ አይጠበቅም:: አይገባምም:: ሰልፋችሁን ማስተካከል አለባችሁ:: አገዛዙን መተው፣ መክዳት:: በልባችሁ ከሸፈታችሁበት በገቢር ልትጎዱት ትችላላችሁ:: ኢሕአፓ ከዚህ ቀደምም ከጭቁን ወታደሮችና መኮንኖች ጎንና አብሮ ሆኖ እንደታገለው ሁሉ ዛሬም ከጎናችሁ ሊቆም ዝግጁ ነው:: ከምር ከፈለጋችሁት ታገኙታላችሁ:: የህዝብ ወታደር ነኝ ታማኝ አገልጋይ እስካላችሁ ድረስ ኢሕአፓም ህዝብም ያዳምጣሉ፣ በጋራ ሆነንም አረመኔውን አገዛዝ አስወግደን የህዝብ ጦር የምትሆኑባትን ኢትዮጵያ በጋራ እንመሰርታለን::

## ለህዝቡ ጥሪ ጆሮአችሁን ክፈቱ፣አድምጡ!!
## ከህዝብ ጎን ተሰለፉ!!
## ድል የኢትዮጵያ ህዝብ ነው!!!